# የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ

**የሚያስፈልጉ ነገሮች**

- መጽሐፍ ቅዱስ፣ ማስታወሻ፣ ደብተርና ጊዜ
- ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች፡- መጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ፣መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትና የአጠናን መመሪያ

**መጀመሪያ**

- ከ20-30 ደቂቃ ያህል ቢቻል ከዚያም በላይ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አስቀሩ፡፡
- በፀሎት ጀምሩ፡፡ በተለይም ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እግዚአብሔር ምሪትን እንዲሰጥህ ፀልዩ፡፡
- ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል ምረጡ፡፡ በመጀመሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ መጽሐፍ በመምረጥ በተከታታይ ማጥናት ጥሩ ነው፡፡ ታዲያ ይህ በእናንተ ምርጫ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ስለ አንድ ታሪክ ወይም ክስተት የሚያወራ ከ10-15 ቁጥር ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምረጡ፡፡ ረጅም ቁጥሮች ያሉትን ምዕራፍ መምረጥ ጭብጥ ሀሳቡን በደንብ እንድትረዱ ስለማያደርግ መምረጥ አያስፈልግም፡፡
- የተመረጠውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል 2 ወይም 3 ጊዜ ደጋግማችሁ አንብቡ፡፡ በመጀመሪያው ዙር በፍጥነት ማንበብ ትችላላችሁ፡፡ በሁለተኛውና በሦስተኛው ዙር ስታነቡ ግን የክፍሉን ዋና ሀሳብ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡
- ሦስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የአጠናን ዘዴዎች፡- ምልከታ (የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)፣ትርጉምና ከሕይወት ጋር ማዛመድ ናቸው፡፡

**ምልከታ (የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት)**

ምልከታ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል ጠቅለል አድርጎ ለመመልከት ወሳኝ የአጠናን ዘዴ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የክፍሉን ጭብጥ ሀሳብ ሳንረዳ ቀጥታ ወደ ትርጉምና ከሕይወት ጋር ማዛመድ እንገባለን፡፡ ነገር ግን ምልከታ በማድረግ የክፍሉን ጭብጥ ሀሳብ የማንረዳ ከሆነ ክፍሉ ለማስተላለፍ የፈለገውን ፍሬ ነገር እናጣለን፡፡ በምልከታ ጊዜ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስህን መጠየቅ አለብህ፡-

- **ማን?**፡- በክፍሉ የተጠቀሰው ማነው? ለማን ነው የተጻፈው? የሚሰማው ጉባኤ ማነው? ይህ በክፍሉ ውስጥ የሚሆነውን ሁሉ ያሳያችኋል፡፡
- **ምን?**፡- በክፍሉ እየሆነ ያለው ምንድነው? ክፍሉ ስለ ምን ያወራል? ክፍሉ የሚያስተምረው ነገር አለ? ለምሳሌ፡- ተአምራት ወይም ፈውስ፣ መምከር፣ማስጠንቀቅ፣ንግግር፣ክርክር፣አለመስማማት፣ውይይት ወዘተ፡፡
- የክፍሉን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ መመልከት ጥያቄ እንድንጠይቅ ይረዳናል፡፡ ይህም ለምሳሌ፡- ክፍሉ ታሪካዊ ክስተት ያወራል? ወይስ ቅኔ ያወራል? ወይስ ሀሳቡን ለመተረክ የተጠቀመ ነው? ወይስ ለሌሎች የተላከ መልዕክት ነው?
- **መቼና የት?**፡- ይህ ጠቃሚ መረጃ ነው፡፡ ይህ ታሪክ መቼና የት እንደከሰተ ራሳችሁን ጠይቁ፡፡ ቦታው የት ነበር ቦታውን ማወቅ ለምን ይጠቅማል? ቀኑ መቼ ነበር? ወሩስ? ዓመቱስ?
- ምልከታ ማድረግ ሌላው ጥቅሙ ራሳችሁን በክፍሉ ውስጥ ባሉ ሰዎች ቦታ አድርጋችሁ እንድትመለከቱ ይረዳችኋል፡፡

***ትርጉም***፡-
አንደኛውን የክፍሉን ጥሩ ዳራ (background) ከገኛችሁ በኋላ እና የክፍሉን ሀሳብ ከተረዳችሁ በኋላ የትርጉም ጥያቄ መጠየቅ ትችላላችሁ፡፡

- **ለምን?**፡- ለምን ተጠቀሰ? ዋና ጉዳዩ ምንድነው? የክፍሉ ዋና ነጥብ ምንድነው?
- በዚህ ጊዜ የክፍሉ ሀሳብ ለመረዳት ቢያስቸግራችሁ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣መጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ያሉ ሌሎች ማጣቀሻዎችን መጠቀም ትችላላችሁ፡፡
- ምልከታና መተርጎም አንዳንድ ጊዜ በተመሳሳይ ጊዜ ሊመጡ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ምልከታና መተርጎም የክፍሉን ሀሳብና ትርጉም እንድትረዱ ያደርጋችኋል፡፡

***ከሕይወት ጋር ማዛመድ***
በመጨረሻ የክፍሉን ሀሳብ ከሕይወት ጋር ካላዛመዳችሁ መጽሐፍ ቅዱስን አጠናን ማለት አትችሉም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ሀሳብ መማርና ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከሕይወታችን ጋር ለማዛመድ ይጠቅመናል፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሳችሁን ጠይቁ፡-

- ይህን ክፍል እንዴት ከሕይወታችን ጋር እናዛምዳለን?
- ከዚህ ክፍል ምን እማራለሁ?
- ይህ ክፍል በግሌ ምን ያስተምረኛል?
- ከሕይወት ጋር ማዛመድ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ከሕይወታችሁና ከልምምዶቻችሁ ጋር እንዲዋሄድ ይረዳል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ከሕይወታችሁ ጋር ስታዋህዱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖራችሁ ከማድረጉም በላይ እግዚአብሔር ለእናንተ ሊናገር የፈለገውን እውነት ከክፍሉ ታገኛላችሁ፡፡

ስለዚህ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴዎችን ካላደረጋችሁ አድርጋችሁ ራሳችሁን ፈትኑ፡፡ በውስጡ ያለውን ምስጢር ስታገኙ በጣም ትደነቃላችሁ፡፡